በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች

የቁጠባና የብድር አገልግሎት ማሠልጠኛ ሰነድ

ሰኔ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ይህ የማሰልጠኛ ሰነድ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አስተባባሪነት እና የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ከስኬት ባንክ፣ ስንቄ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በተውጣጡ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው አመራሮችና ባለሙያዎች የተዘጋጀ ነው።

	አዘጋጅ		
ተ.ቁ	**ስም**	**ሚና**	**ተቋም**
1	አቶ ሲራክ ማሞ ኃይለመለኮት	አስተባባሪ	ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት
2	አቶ አሰፋው ሁንዱማን	አባል	ስንቄ ባንክ
3	አቶ ፍሬው ተስፋዬ	አባል	ስኬት ባንክ
4	አቶ የሺድንበር ላቀው	አባል	ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

ማውጫ

I. መግቢያ 1
የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተልዕኮ፣ ራዕይና ዕሴቶች 2
ክፍል አንድ 3
1.1. ትርጓሜ 3
1.2. ዓላማ 4
1.2.1. ጥቅል ዓላማ 4
1.2.2. ዝርዝር ዓላማ 4
1.3. አስፈላጊነት 4
1.4. መርሆዎች 5
1.5. ስልጠናው የሚሠጥበት ስልት 5
1.6. ከሥልጠናው የሚጠበቁ ውጤቶች 6
ክፍል ሁለት 7
2. የፋይናንስ አገልግሎትና የድጋፍ አቅርቦት ስርዓት 7
2.1. የቁጠባና ብድር አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተቋማት 7
2.2. በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የሚሠጡ አገልግሎቶች 9
2.3. የቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት 10
2.3.1. የቁጠባ አይነቶች 11
2.3.2. በቁጠባ ሂሳብ ላይ ስለሚከፈል ወለድና የአወጣጥ ስርዓት 13
2.3.3. የቁጠባ ምንጮች 13
2.4. የብድር አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት 14
2.4.1. የብድር ዓይነቶች 14
2.4.1.1. ጊዜ ላይ የተመሰረተ ብድር 14
2.4.1.2. የኦቨር ድራፍት ብድር 14
2.4.1.3. ኦቨር ድሮዋል 15
2.4.1.4. ለማስመጣት የሚሰጥ የመተማመኛ ሰነድ (ሌተር ኦፍ ክሬዲት) 15
2.4.1.5. የባንክ የዋስትና ብድር 15
2.4.2. በወለድ የሚሠጥ የብድር አገልግሎት 15
2.4.3. ወለድ አልባ የብድር አገልግሎት 16
2.4.4. የብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎች 16
2.4.5. ብድር ለማግኘት የተቀመጡ ቅድመ-ሁኔታዎች 17
2.5. የቅድመ-ብድር ተግባራት 17
2.5.1. የማስተዋወቅ ሥራ 17
2.6. የንግድ ሥራ ዕቅድ ማቅረብ 18

2.7. ከብድር አመልካቾች የሚጠበቁ ማሥረጃዎች 19

2.8. የብድር ዋስትና አይነቶች 20

2.8.1. በመንግስት የሚሸፈን የብድር ዋስትና 20
2.8.2. የሦስትዮሽ ውል ስምምነት 20
2.8.3. የቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና 21
2.8.4. የደመወዝ ዋስትና 21
2.8.5. የመጋዘን አገልግሎት ዋስትና 21
2.8.6. የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት (Second level land certificate) 21
2.8.7. የጊዜ ገደብ ቁጠባ ዋስትና (fixed time deposit) 21
2.8.8. የአክሲዮን ምስክር ወረቀት 21

2.9. የብድር መጠን 21

2.10. በዋስትና የተያዘ ንብረት የመድን ሽፋን 22

2.11. የብድር ውል መፈጸም 22

2.12. ብድር ማሰራጨት 22

2.13. የአገልግሎት ክፍያ 22

2.14. የብድር ወለድ ምጣኔ 22

2.15. የእፎይታ ጊዜ 22

2.16. የብድር መመለሻ ጊዜ 23

ክፍል ሦስት 24

3. ድህረ-ብድር ተግባራት 24

3.1. ለኢንተርፕራይዞች የሚደረግ ድጋፍና ክትትል 24

3.2. ብድር ማስመለስ 25

3.3. ማበረታቻ 25

3.4. ቅጣት 25

ክፍል አራት 26

4. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት 26

4.1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ 26

4.2. ገንዘብ ሚኒስቴር 26

4.3. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር 26

4.4. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት 27

4.5. ስራና ክህሎት ሚኒስቴር 27

4.6. የክልል መንግስት፣ የከተማ እና ወረዳ አስተዳደሮች 28

4.7. የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት 28

4.8. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት 28
4.9. በክልል፣ በዞን በከተማና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የዘርፉ ልማት አደረጃጀቶች 28
ክፍል አምስት 30
5. የድጋፍ፣ ክትትል እና የግምገማ ስርዓት 30
5.1. የክትትልና ድጋፍ አደረጃጀት 30
5.2. የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት እና ልውውጥ 31
5.3. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 31
ማጣቀሻ ሰነዶች፣ 32
አባሪዎች 33

I. መግቢያ

ሀገራችን በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለመሆን በምታደርገው ጥረት ዋነኛ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ልማት በማፋጠን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን ማረጋገጥ አንዱ ነው።

ለዚህም የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱ ያሉበትን ማነቆዎች በጥናት ለይቶና ያንን ሊፈቱ የሚችሉ አሰራሮችን ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረጉ መሄድን ይጠይቃል። በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ማዕቀፍ ውስጥ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ካሉባቸው ማነቆዎች መካከል አንዱ የስራ ማስኬጃ ብድር ማግኘት አለመቻል ሲሆን ይህም በምርታማነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳረፍ በዋጋና በአቅርቦት ጊዜ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋል።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ መሰረት በአገራችን በአሁኑ ሰዓት የቁጠባ እና የብድር አገልግሎት የሚሠጡ 32 ባንኮች እና 50 ማይክሮፋይናንስ ተቋማት የሚገኙ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየተበራከተ መምጣቱ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን በድጋፉ ተደራሽ በማድረግ ሂደት አወንታዊ አስተዋጽዖ መጫወት እንዲችል ያደርገዋል። በብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ (እ.ኤ.አ. 2021 - 2025) ሰነድ ላይ ባንኮችና ማይክሮፋይናንስ ተቋማት እ.ኤ.አ. በ2020 ለግል ዘርፉ ካሰራጩት ብድር ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያሰራጩት የመቶኛ ድርሻ ከ5% አይበልጥም። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የ2021/22 እ.ኤ.አ. ሪፖርት መሰረት የፋይናንስ ተቋማት ከሠጡት ብድር ለኢንዱስትሪ ዘርፉ ያሰራጩት 12.2 በመቶ ነው። ይህም ዘርፉ የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር ያለበት ለመሆኑ አመላካች ነው። በአንጻሩ በአሁኑ ሰዓት መንግስት በአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እንዲሁም ዲጂታል ኢትዮጵያን (2025) ለማሳካት ትኩረት መሠጠቱ፣ ለኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚሰራጨው ብድር ወደ 24 በመቶ እንዲያድግ አቅጣጫ መቀመጡ፤ በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ መሰረተ-ልማትን እና ኢኖቬቲቭ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት በዕቅድ የያዛቸው ተግባራት በቀጣይ ለሚኖረው የብድር ተደራሽነት ማደግ የራሱን አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

የፋይናንስ ተደራሽነት ችግርን ለመፍታት መንግስት የብድር አቅርቦት ስነ-ምህዳሩን ምቹ ለማድረግ እየሰራቸው ካሉ ተግባራት ጎን ለጎን የቁጠባ ባህልን የማሳደግ እና የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን የማበደር አቅም የማጎልበት ስራዎች አስፈላጊ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፋይናንስ ተቋማት እና በየደረጃው ያለው የመንግስት አካል በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር ተደራሽ ለማድረግ ከግንዛቤ ማስጨበጥ እስከ ብድር ማስመለስ በትብብርና በቅንጅት መስራት ይገባል።

በመሆኑም የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት ተግዳሮት የሆነውን የብድር አቅርቦት ችግር በመፍታትና የአምራች ዘርፉን ልማት በማፋጠን በአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገቱ ውስጥ

ዘርፉ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ የቁጠባና ብድር አቅርቦት ስርዓቱን ምንነት፣ የብድር ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ስላለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎችና በሂደቱ በሚኖረው የአስፈጻሚና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ለአስፈጻሚ አካላት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በደንብ ቁጥር 526/2015 አንቀጽ 5(2) በተሰጠው ስልጣና መሰረት ይህንን የቁጠባና ብድር አገልግሎት ማስልጠኛ ሰነድ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም በፋይናንስ ተቋማት የሚሠጡ አገልግሎቶች፣ ድህረ-ብድር ተግባራት፣ በሂደቱ ሊኖር የሚገባውን የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት እና የክትትል ድጋፍና ግምገማ ስርዓትን ያካተተ ነው።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተልዕኮ፣ ራዕይና ዕሴቶች

ተልዕኮ

የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀትና በመተግበር፤ የባለድርሻ አካላትንና የአምራች ኢንተርፕራይዞችን አቅም በመገንባት፤ ሁሉን አቀፍና ውጤታማ ድጋፎችን በመስጠት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር በማድረግ ገቢ ምርቶችን መተካት፤ የኤክስፖርት አቅምን ማሳደግ፤ የስራ እድልን ማስፋትና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የዘርፉን ድርሻ ማሳደግ፤ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ።

ራዕይ

በ2022 በአፍሪካ የተወዳዳሪነት ተምሳሌት የሆነና በአገራችን ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ ያለው የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ዘርፍ ተገንብቶ ማየት!

ዕሴቶች

- ታታሪ፣ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሃብት ማፍራት፤
- ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን፤
- ለቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መትጋት፤
- የተሳለጠ ቅንጅታዊ አሰራር ማስፈን፤
- አዳዲስ አሠራርና ፈጠራን ማበረታታት፤
- እድገት፣ ጥራትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማበረታታት፤
- አሳታፊነት፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤
- በአገር ምርት መኩራት፤
- ተአማኒ፤ ተደራሽና ወቅታዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት፤
- ለማያቋርጥ ለውጥ ዝግጁ መሆን፤

ክፍል አንድ

1.1. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው እስካልሆነ በስተቀር በዚህ ማስፈጸሚያ ሰነድ ውስጥ፤

1. **"የፋይናንስ አቅራቢ ተቋም"** ማለት ባንክ፣ አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋም፣ የሃዋላ ድርጅት ወይም በብሄራዊ ባንክ የሚወሠን ሌላ ተመሣሳይ ተቋም ነው፡፡
2. **"የብድር ዋስትና"** ማለት ለሚወሰድ ብድር በዋስትና የሚቀርብ የንብረት፣ የመጋዘን አገልግሎት፣ የመንግስት ዋስትና ፈንድ ፣ የደመወዝ መያዣ/ዋስትና ነው፡፡
3. **"የተንቀሳቃሽ ንብረቶች ዋስትና"** ማለት ኢንተርፕራይዙ ለሚወሰደው ብድር በዋስትና የሚቀርብ ከመሬት፣ ቤትና ህንጻ ውጭ ያለ ንብረት ነው፡፡
4. **"የግዴታ ቁጠባ"** ማለት በተቋሙ የብድር ደንበኞች የሚያስቀምጡትና ያለባቸውን የብድር ዕዳ ከፍለው እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ሊወጣ የማይችል ቁጠባ ሲሆን የቅድመ ብድር ቁጠባና ድህረ ብድር ቁጠባ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡
5. **"የውዴታ ቁጠባ"** ማለት በአበዳሪ ተቋሙ የብድር ደንበኞችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም ተቋማት በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚቀመጥ የቁጠባ ዓይነት ሲሆን አስቀማጮቹ በፈለጉ ጊዜ ወጪ ሊያደርጉት የሚችሉት ቁጠባ ነው፡፡
6. **"ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም በጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት የሚያመርት ነው፡፡
7. **"አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 11 እስከ 50 ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 600,001 እስከ ብር 10 ሚሊዮን ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤
8. **"መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 51 እስከ 100 ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 10,000,001 እስከ 90 ሚሊዮን ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤
9. **"ነባር ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ህጋዊ ፈቃድ አግኝቶ ወደ ሥራ ከገባ አንድ ዓመት እና በላይ የሆነው ነው፡፡
10. **"አዲስ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ህጋዊ ፈቃድ አግኝቶ ወደ ሥራ ከገባ አንድ ዓመት ያልሆነው ነው፡፡

11. **"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት"** ማለት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ችግር የለየና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የተሟላ መረጃ የማደራጀትና የመስጠት፣ ስልጠናና ምክር፣ ቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት፣ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያና ሌሎች መሰል ድጋፎችን መስጠትን እንዲሁም በተለያዩ ተቋማት የሚሠጡ አስፈላጊ ድጋፎችን ማመቻቸትን የሚያካትት ድጋፍ ነው፡፡

12. **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 47 የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

13. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

1.2. ዓላማ

1.2.1. ጥቅል ዓላማ

ለአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ አስፈጻሚ አካላት አመራሮችና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ኢንተርፕራይዞች ስለ ቁጠባና ብድር ያላቸው ግንዛቤና እውቀት እንዲሻሻል፣ እንዲቆጥቡ እና ብድር አግኝተው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አስቻይ ሁኔታ መፍጠርና የተሻለ የብድር አመላለስ እንዲኖር መስራት ነው፡፡

1.2.2. ዝርዝር ዓላማ

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፉን ለሚደግፉ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን መገንባትና ከግንዛቤ ፈጠራ እስከ ብድር ማስመለስ በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
- ስለ ቁጠባ ግንዛቤ በማስጨበጥ የሚሰበሰብ ቁጠባን ማሳደግ እና የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን የማበደር አቅም እንዲሻሻል ማድረግ፤
- ኢንተርፕራይዞች ስለ ቁጠባና ብድር ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ እንዲቆጥቡ ማስቻልና የብድር ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፤
- የብድር አመላለስ ምጣኔን በማሳደግ ጤናማ የብድር ስርዓት እንዲፈጠር መስራት፤

1.3. አስፈላጊነት

- የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማትን የሚደግፉ ባለሙያዎች ስለ ቁጠባና ብድር አገልግሎቱ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑና ይህን በማሻሻል ዘርፉን በአገልግሎቱ ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ፣

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የቁጠባ ባህል ዝቅተኛ መሆኑና በፋይናንስ ተቋማት ብድር ለማግኘት ቁጠባ አንዱ መስፈርት በመሆኑ ይህንን ችግር መሻገር አስፈላጊ በመሆኑ፣
- የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለዘርፉ ልማት በስፋት ብድር ለማቅረብ የፋይናንስ አቅም ውስንነት ያለባቸው መሆኑና ቁጠባ ላይ በስፋት በመስራት የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን የማበደር አቅም ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑ፤
- ባንኮችና ማይክሮፋይናንስ ተቋማት ካሰራጩት ብድር ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተሰራጨው አነስተኛ መሆኑ (ለግል ዘርፉ ከተሰጠው ከ5% ያልበለጠ) እና በዘርፉ ጥናት ሲደረግ የብድር አቅርቦት ችግር ግንባር ቀደም ሆነው ከሚጠቀሱ የኢንተርፕራይዝ ችግሮች አንዱ መሆኑና ይህ በፋይናንስ ተቋማት እንዲሟላ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ፤
- ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ከግንዛቤ ፈጠራ እስከ ብድር ማስመለስ ያሉ ተግባራትን በመተባበር እና በመቀናጀት እየሰሩ ባለመሆኑ ይህንን ማድረግ የሚችሉበት አሰራር መፍጠር፤

1.4. መርሆዎች

1) የብድር አገልግሎቱ ቁጠባ መር ይሆናል፡፡
2) የብድር አገልግሎቱ ከፍተኛ የማደግ አቅም እና አዳዲስ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው እንዲሁም ለኤክስፖርት ወይም ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱ የሥራ ዘርፎች ላይ ተሠማርተው በሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ የሚሠጥ ይሆናል፡፡
3) የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የብድር ገንዘብ ምንጫቸው በአብዛኛው ከቁጠባ ይሆናል፡፡
4) የብድር አመላለስ ምጣኔውም መቶ በመቶ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
5) የቁጠባና ብድር አገልግሎት ሥርዓቱ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ይሆናል፡፡
6) የተቀረጹ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና ህጎችን በማክበር ይሰራል፡፡

1.5. ስልጠናው የሚሠጥበት ስልት

በዚህ የማሰልጠኛ ሰነድ ላይ ለአዳዲስ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት መካከለኛ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ለክልል እና ከተማ አስተዳደሮች አመራሮችና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት እና የዞን፣ የከተሞችና የወረዳዎችን የዘርፉ ልማት መዋቅር አመራርና ባለሙያዎችን ስልጠና እንዲሠጡ በመከታተል እና በመደገፍ፤ በታችኛው የዘርፉ የአደረጃጀት እርከን ላይ የሚገኙና ስልጠና የወሰዱ አመራችና ባለሙያዎች ለኢንተርፕራይዞች ስልጠና እንዲሰጡ በማድረግ ይፈጸማል፡፡ ስልጠናውን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ከባንኮች እና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ፕረዘንቴሽን በማቅረብ፣ በቡድን ውይይት፣ በፋይናንስ ተቋም ቅርንጫፍ በአካል በመገኘትና በመጎብኘት የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

1.6. ከሥልጠናው የሚጠበቁ ውጤቶች

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም የዘርፉ መዋቅር አመራርና ባለሙያዎች ያላቸውን ግንዛቤና ዕውቀት ማሳደግና ስራቸውን ለማሳካት እና ችግር ለመፍታት አዳዲስ ስልቶችን እንዲጠቀሙ ማስቻልና የሚታይ የባህሪ ለውጥ ማምጣት፤
- ቁጠባ ለማሰባሰብ እና የብድር አቅርቦት በማመቻቸት ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ለማድረግ የተያዙ ግቦችን በማሳካት ለዘርፉ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት አወንታዊ ሚና መጫወት፤

ክፍል ሁለት

2. የፋይናንስ አገልግሎትና የድጋፍ አቅርቦት ስርዓት

2.1. የቁጠባና ብድር አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተቋማት

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ መሰረት 32 ንግድ ባንኮች እና 50 ማይክሮፋይናንስ ተቋማት በስራ ላይ የሚገኙ ሲሆን እ.ኤ.አ. ከ2018/19 እስከ 2021/22 ድረስ ባንኮች ብር 260 ቢሊዮን እንዲሁም ማይክሮፋይናንስ ተቋማት ብር 48 ቢሊዮን ለግል ዘርፉ በብድር አቅርበዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እ.ኤ.አ. በ2021/22 ከተሰራጨው ብድር ለኢንዱስትሪ ዘርፉ የተሰጠው ብድር 12.2 በመቶ ሲሆን ይህንን ድርሻ ወደ 24 በመቶ ከፍ ለማድረግ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑን ተከትሎ የብድር አገልግሎት የሚሠጡ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን ለይቶ ከቁጠባ ማሰባሰብ እስከ ብድር ማስመለስ በቅንጅት መስራትና የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የተጠቃሚነት ድርሻ ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡ ካሉት ባንኮች ውስጥ 6 የሚሆኑት ከማይክሮፋይናንስ ተቋምነት ወደ ባንክ ያደጉ ሰሆን ይህም ከአዳዲስ ደንበኞቻቸው በተጨማሪ ቀደም ሲል ሲያገለግሏቸው የነበሩትን ደንበኞች ከፍ ያለ የብድር ፍላጎት ለማሟላት ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና ደንበኝነታቸውን በማዝለቅ ዘርፉን ተጠቃሚ እንዲሆን አዎንታዊ ሚና መጫወት ያስችላቸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚሠጡ ባንኮችና ማይክሮፋይናንስ ተቋማት

ተ.ቁ	ማይክሮፋይናንስ ተቋማት	ባንክ	ምርመራ
1	ሸገር ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ሰኬት ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
2	ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም	ስንቄ ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
3	ግራንድ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ	
4	የምስራች ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አባይ ባንክ አክሲዮን ማህበር	
5	ልዩ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር	
6	ጋሻ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አዋሽ ባንክ	
7	አፍሪካ ቪሌጅ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አቢሲኒያ ባንክ	
8	ቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ብርሃን ባንክ	
9	ፒስ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ቡና ባንክ	
10	ንስር ማይክሮፋይናንስ ተቋም	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	
11	እሸት ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ	
12	ዋሳሳ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ዳሸን ባንክ	
13	ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ	
14	ቀንዲል ማይክሮፋይናንስ ተቋም	እናት ባንክ	

ተ.ቁ	ማይክሮፋይናንስ ተቋማት	ባንክ	ምርመራ
15	መተማመን ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ	
16	ድሬ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ኦሮሚያ ባንክ	
17	አጋር ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ህብረት ባንክ	
18	ሀርቡ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ወጋገን ባንክ	
19	ድጋፍ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ዘመን ባንክ	
20	ሀረሪ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	
21	ለፋይዳ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ዘምዘም ባንክ	
22	ተስፋ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ሂጅራ ባንክ	
23	ጋምቤላ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ሸበሌ ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
24	ዳይናሚክ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አማራ ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
25	መክሊት ማይክሮፋይናንስ ተቋም	አሐሁዱ ባንክ	
26	ደቦ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ፀደይ ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
27	ቀርሺ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ፀሀይ ባንክ	
28	አፋር ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ገዳ ባንክ	
29	ራይስ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ዘምዘም ባንክ	
30	አደዳይ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ራሚስ ባንክ	
31	ልደታ ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ኦሞ ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
32	ቪዥን ማይክሮፋይናንስ ተቋም	ሲዳማ ባንክ	ከማይክሮፋይናንስ ያደገ
33	ጎግባ ማይክሮፋይናንስ ተቋም		
34	ካፊ ማይክሮፋይናንስ ተቋም		
35	ሳሃል ማይክሮፋይናንስ ተቋም		
36	ዋን ማይክሮፋይናንስ ተቋም		

ማስታወሻ፦ መረጃው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ድረ-ገጽ ላይ የተወሰደ ሲሆን በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ ባንኮች እና ማይክሮፋይናንስ ተቋማት ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሳቢ ይደረግ፤

2.2. በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የሚሠጡ አገልግሎቶች

ከተቋም ተቋም ልዩነት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ባንኮች እና ማይክሮፋይናንስ ተቋማት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉባቸው የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሠጣሉ፡፡ ከእነዚህ አገልግሎቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

i. የቁጠባ አገልግሎት፣
ii. ጊዜ ላይ የተመሰረት ብድር አገልግሎት፣
iii. የአነስተኛ መድህን አገልግሎት፣
iv. የሃዋላ አገልግሎት፣
v. የውጭ ምንዛሬ አገልግሎት፣
vi. የዲጂታል ባንክ አገልግሎት፣
   - ✓ የኤ.ቲ.ኤም አገልግሎት፣
   - ✓ የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት፣
   - ✓ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት
vii. የባንክ ዋስትናዎች (Advance Guarantees)
viii. የኦቨር ድራፍት ብድር (ከተቀማጭ ሂሳብ ላይ የሚሰጥ)፣
ix. ለማስመጣት የሚሠጥ የመተማመኛ ሰነድ (ሌተር ኦፍ ክሬዲት)፣
x. የሦስተኛ ወገን ገንዘብ ማስተዳደር አገልግሎት፣
   - ✓ የገንዘብ አስተዳደር አገልግሎት፡- የደመወዝ፣ የጡረታ፣ የግብር፣ የመብራት፣ የውሃ ወዘተ ክፍያ አገልግሎቶችን ያካትታል፡፡
xi. ገንዘብ ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች፣
   - ✓ የሒሳብ አያያዝ እና የፋይናንስ ሥራ አመራር ሥልጠና አገልግሎት፣
   - ✓ የፋይናንስ አጠቃቀም እና አስተዳደር ምክር አገልግሎት፣

2.3. የቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

በአንድ አካባቢ፣ በአገር አቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚከወን የልማት ስራ ገንዘብ ከሚገኝባቸው መንገዶች ዋነኛው ቁጠባ በመሆኑ ቁጠባን ከልማት በስተጀርባ ያለ ሞተር አድርጎ መውሰድ ይቻላል። በቁጠባ የተገኘ ገንዘብ ወደ ኢንቨስትመንት ሲገባ ምርትን በማሳደግ ገቢ ያመጣል። በዚህ መንገድ የተገኘው ገቢ በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ የአኗኗር ዘይቤን በማሻሻል እድገትን እውን ለማድረግ ያግዛል። ከዚህ አኳያ ቁጠባን የማሰባሰብ ተግባር መልሶ በስራ ላይ ከማዋል ባሻገር ለመበደር እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚጠየቅ ከሆነ ለኢንቨስትመንት የሚውል የብድር ተደራሽነትን ከማስፋት ባልተናነሰ መልኩ ሊታይ ይገባል።

ቁጠባ ለብድር ሊውል የሚችል ገንዘብ አንዱ ምንጭ በመሆን፣ የታቀደም ይሁን ያልታቀደ የወደፊት ወጪን የመሸፈን አቅም በመፍጠር፣ ደንበኛ ለተበዳሪነት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ በመሆን፣ ከወለድ ገቢ በማስገኘት፣ ደንበኛ ከባንክ ሥርዓት ጋር ያለው ቁርኝት እንዲዳብር ወዘተ በማድረግ ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው። አበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት በማንኛውም ጊዜ የሚቀርብን የብድር ጥያቄ እንዲሁም አስቀድመው ያልታቀዱ ወጪዎችን ማስተናገድ የሚችል የገንዘብ አቅም እንዲኖራቸው በአንድ በተወሰነ ጊዜ በብድር የሚያሰራጩትን ገንዘብ እና በተመሳሳይ ጊዜ ከቁጠባ የሚሰበስቡትን ገንዘብ ምጣኔ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። የተሰራጨ ብድር ከቁጠባ አኳያ ሊኖረው የሚገባውን ምጣኔ (Loan to Deposit Ratio = Total Loan/ Total Deposit) በተመለከተ ጥሩ የሚባለው ብድሩ የቁጠባውን ከ80 እስከ 90 በመቶ ባይበልጥ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።

በአንጻሩ በአገራችን ባንኮችና ማይክሮፋይናንስ ተቋማት እ.ኤ.አ. ከ2018/19 እስከ 2021/22 ካሰራጩት ብድር በአማካይ 76 በመቶ የሚሆነውን ብቻ ከቁጠባ እንደሰበሰቡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ ሪፖርት የመላክታል። ይህም ቁጠባ በማሰባሰብ በኩል ብዙ መስራት እንዳለብን የሚያሳይ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ (እ.ኤ.አ. 2021 - 2025) ከአዋቂ ሰዎች (adults) መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ያላቸው 45% (2020) እንዲሁም የፋይናንስ ተቋማት ስለሚሰጡት አገልግሎቶች ግንዛቤ ያላቸው 47% (2019) ብቻ እንደሆኑ ያመላክታል። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚሁ ስትራቴጂ ውስጥ እ.ኤ.አ. በ2025 መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ያላቸውን እና ስለ ፋይናንስ ግንዛቤ ያላቸውን አዋቂ ሰዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 70 እና 75 ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሃገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ለመተግበር የሚሰሩ ስራዎች፣ የፋይናንስ መሰረተ-ልማቶች መስፋፋት እና ኢኖቬቲቭ የሆነ አገልግሎቶች መጀመር ቁጠባን በማሻሻል ረገድ የራሱ ሚና ሊጫወት ይችላል።

እንደ አጠቃላይ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያገኙትን ገቢ በማብቃቃት እንዲሁም ወጪን በመቀነስ ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ካፒታል ለማሣደግና ለተለያዩ ወጪዎች የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ በብድር ለማግኘት ቅድመ-ሁኔታውን ለማሟላት እንዲሁም ጥሪት ለመያዝ በመርህ ደረጃ ቁጠባን እንደ ባህል መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እና በየደረጃው የዘርፉን ልማት የሚያስተባብሩ መዋቅሮች፡-

1. የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ተደራሽ ባልሆኑባቸው የከተማ/ወረዳ/የቀበሌ አስተዳደር መዋቅሮች ንዑስ ጽ/ቤት ወይም ቅርንጫፍ በመክፈት እና በአካባቢያቸው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና በመስጠት፤
2. ቁጠባን የሚያበረታታ ማራኪ የቁጠባ ወለድ፣ ወለድ አልባ እና ተጨማሪ የቁጠባ አሠባሰብ ሥልቶችን በመቅረፅ፤
3. የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ የቁጠባ ምንጮችን በመለየት ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ትኩረት ሰጥቶ በቅንጅት በመስራት፤
4. በከተማ/ወረዳ/ቀበሌ አስተዳደር መዋቅር ለተወሠነ ጊዜ ያለሥራ የሚቀመጥ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ያላቸው ተቋማትን በመለየት በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማቱ ተቀማጭ በማድረግና ሌሎች አውት ሶርስ ሊደረጉ የሚችሉ የፋይናንሻል ሥራዎች በተቋማቱ በኩል እንዲሠሩ በማድረግ፤
5. በተራ ቁጥር 4 ላይ በተለገለጸው መንገድ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ብድር ብቻ እንዲያውል የሚያደርግ አሰራር አስቀምጦ በመተግበር፤

ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ሥራ ማሥጀመሪያ ወይም ማሥፋፊያ የሚውለውን ገንዘብ መሰብሰብ እና የማበደር አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ይቻላል፡፡

2.3.1. የቁጠባ አይነቶች

የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች ሊገኝ የሚችለውን ገንዘብ ለመሰብሰብ የተለያዩ የቁጠባ አይነቶችን የሚጠቀሙ ሲሆን በጥቅሉ የግዴታ ቁጠባ እና የውዴታ/ፈቃድ ቁጠባ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የቁጠባ አማራጮችን ከወዲሁ አውቀው እንዲቆጥቡ ለማድረግ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያሥፈልጋል፡፡

2.3.1.1. የግዴታ ቁጠባ

- ***ቅድመ-ብድር ቁጠባ፦*** ይህ ቁጠባ ብድር የሚፈልጉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለብድር አገልግሎቱ ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በሚከፈት የቁጠባ ሂሳብ የሚቆጠብ ቁጠባ ነው። ይህ ቁጠባ በአንድ ጊዜ ወይም በሂደት ገቢ ሊደረግ ይችላል።

- ***በብድር ቆይታ ጊዜ ውስጥ የሚሰበሰብ የግዴታ ቁጠባ፦*** ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ተበዳሪ የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር ከፍለው እስከሚያጠናቅቁ ጊዜ ድረስ የግዴታ መደበኛ ቁጠባ እንዲቆጥቡ የሚደረግበት ነው። ይህም ተበዳሪው ጸድቆ በተሰጠው የብድር መጠን መሰረት በየወሩ የሚቆጠብ ሆኖ ቁጠባውም ብድሩ በተሰጠ በወሩ መሰብሰብ ይጀምራል።

2.3.1.2. የውዴታ/ፈቃድ ቁጠባ አይነቶች

ማንኛውም ተበዳሪም ሆነ ተበዳሪ ያልሆኑ ግለሰቦች፣ የኢንተርፕራይዝ ባለቤቶች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ወደ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በመሄድ መቆጠብ ይችላሉ። የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማቱ የአገልግሎት ተደራሽነታቸውን ይበልጥ ለማስፋት እንዲሁም የብድር ገንዘብ አቅርቦትን ለማሳደግ ከዚህ በታች በዝርዝር የተጠቀሱ የውዴታ ቁጠባ አይነቶችን በመተግበር ላይ ሲሆኑ ይህንንም ለህብረተሰቡ የማስተዋወቅ ስራ በማከናወን የቁጠባ ክምችትን ከማሳደግ ባለፈ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲቆጥቡ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

- **የተቀማጭ/የደብተር ቁጠባ ፦** ይህ ቁጠባ ደንበኞች የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የሚያስቀምጡትን መነሻ ገንዘብ በፋይናንስ ተቋሙ በሚከፍቱት አካውንት በሚፈልጉት ጊዜ መቆጠብ እና ማውጣት የሚችሉበት የቁጠባ ዓይነት ነው።

- **በጊዜ ገደብ የሚቀመጥ ቁጠባ ፦** ይህ የቁጠባ ዓይነት በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ አስቀማጩ ደንበኛ ከፋይናንስ ተቋሙ ጋር በሚያደርገው የውል ስምምነት መሠረት የሚወሰንበት እና የወለድ ምጣኔው በተቋሙ ውስጥ በሚቆይበት የውል ሥምምነት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ተሰልቶ የሚከፈልበት ቁጠባ ነው። ቁጠባው ከውል ሥምምነቱ በፊት ወጪ የሚደረግ ከሆነ አስቀማጩ ወይም ደንበኛው በውል ስምምነቱ የተገለጸውን ወለድ እንዲያጣ ሆኖ ወለዱ በመደበኛው ምጣኔ ታስቦ ገንዘቡን ወጪ ማድረግ ይችላል።

- **ወለድ የማይታሰብለት ቁጠባ ፡-** ይህ የቁጠባ ዓይነት ኢንተርፕራይዞች፣ ግለሰቦች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ገንዘባቸውን በአደራ መልኩ የሚያስቀምጡበት ነው፡፡
- **የሳጥን ቁጠባ፡-** የንግድ ተቋማት እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅት ሠራተኞች፣ የብድር ደንበኞች እና ማንኛውም ግለሰብ ከአበዳሪ የፋይናንስ ተቋሙ ለዚሁ ተግባር በሚቀርበው የቁጠባ ሳጥን ውስጥ ገንዘብ የሚቆጥቡበት የቁጠባ ዓይነት ነው፡፡

2.3.2. **በቁጠባ ሂሳብ ላይ ስለሚከፈል ወለድና የአወጣጥ ስርዓት**

2.3.2.1. የወለድ ሥሌት

ደንበኞች በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለሚያስቀምጡት ገንዘብ በፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ በኩል ወለድ ይከፈላቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ደንበኛው የወለድ አገልግሎትን የማይፈልግ ከሆነ ለዚሁ ተብሎ በተዘረጋ የወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ይስተናገዳል፡፡ ወለድ የሚከፈልበት ቁጠባ ለሚቆጥቡ ደንበኞች በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለተቀመጠ ተቀማጭ ቁጠባ የሚከፈለው የወለድ ምጣኔ የሚወሰነው በየጊዜው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋም በሚያወጣው የማስፈጸሚያ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

2.3.2.2. የቁጠባ አወጣጥ ሥርዓት

- የቅድመ-ብድር ቁጠባዎች እንደ ጋርዮሽ ገንዘብ (Matching Fund) የሚያገለግሉ በመሆናቸው ወጪ መሆን የሚችሉት ተበዳሪው ለብድር ብቁ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን ተበዳሪው በቆጠበው የቁጠባ መጠን እና በንግድ እቅዱ መሠረት በጸደቀለት ብድር የቁጠባ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት መውሰድ ይችላል፡፡
- በብድር ቆይታ ጊዜ ውስጥ የሚቆጠበው የግዴታ ቁጠባ ወጪ መሆን የሚችለው ብድሩ ተጠቃልሎ ሲከፈል ይሆናል፡፡
- ደንበኞች በውዴታ የቆጠቡትን ገንዘብ በፈለጉት ጊዜ ወደ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ቀርበው ወጪ ማድረግ ይችላሉ፡፡

2.3.3. **የቁጠባ ምንጮች**

የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በየደረጃው ከሚገኘው የዘርፉ ልማት መዋቅርና ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ያሉትን የቁጠባ ምንጮች አሟጠው መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቋማቱ የማበደር አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ከዚህ በታች በዝርዝር የተቀመጡ ዋና ዋና የፋይናንስ ምንጮችን መሠረት በማድረግ ቁጠባ ሊሰበስቡ ይችላሉ፡፡

- በየአካባቢው የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣

- የከተማ/የወረዳ አስተዳደር ተቋሞች ለግንባታዎች ከኮንትራክተሮች በቅድሚያ የሚያስከፍሉት ሪቴንሽን፣
- በየአካባቢው ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የተሰባሰበ ገንዘብ፣
- በየአካባቢው ከሚገኙ የተለያዩ የህዝብ አደረጃጀት ተቋማት፣ ዕድሮች እና የዕቁብ ማህበራት፣
- የውስጥ ገቢ ካላቸው የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና እና የውሃ ተቋማት፣
- በየአካባቢው ካሉ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣
- የግል ባለሀብቶች እና በክላስተር አደረጃጀት የሚሰሩ ኢንተርፕራይዞች፣
- ተበዳሪ ካልሆኑና የመንግስት ፕሮጀክት ሥራዎችን በውል መሠረት ከሚሰሩ ኢንተርፕራይዞችና መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፤

2.4. የብድር አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት

ብድር ማለት አንድ አካል በተለይም እንደ ባንክ ያለ የፋይናንስ ተቋም ለሌላ አካል ብዙ ጊዜ ለግለሰብ ወይም ለንግድ ድርጅት በስምምነት በሚቀመጥ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ ገንዘብ የሚሠጥበት የፋይናንስ አቅርቦት ስርዓት ሲሆን ከወለድ ነጻ የሚሠጥ ካልሆነ በስተቀር የብድር ተመላሹ ወለድን ጨምሮ ክፍያ የሚፈጸምበት አሰራር ነው፡፡

2.4.1. የብድር ዓይነቶች

2.4.1.1. ጊዜ ላይ የተመሰረተ ብድር

ይህ የብድር ዓይነት ደንበኞች ቀድመው በተዋዋሉት ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ እና ወለድ የሚከፈልበት ነው፡፡ ይህ የብድር ዓይነት ከሚመለስበት ጊዜ አኳያ በሦስት ሊከፈል ይችላል፡፡

- **የአጭር ጊዜ ብድር**፡- ይህ ብድር በአብዛኛው ለስራ ማስኬጃ የሚውል ሲሆን ብድሩ ከ 2 ዓመት ባነሰ ጊዜ ተመልሶ የሚከፈል ነው፡፡ ይህ ብድር በአብዛኛው ደመወዝ ለመክፈል፣ የግል ወጪ ለመሸፈን ወዘተ የሚውልና የአጭር ጊዜ የገንዘብ ፍላጎትን ለማሟላት የሚጠቅም ነው፡፡
- **የመካከለኛ ጊዜ ብድር**፡- የመካከለኛ ጊዜ ብድር ደግሞ ከ2 ዓመት እስከ 5 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ የሚቆይ፣ በአብዛኛው ለንግድ ስራ የሚውል እና ማሽነሪ እና መገልገያ መሳሪያዎች ለመግዣ፣ ለማስፋፊያ፣ ለስራ ማስኬጃ ወዘተ የሚውል ብድር ነው፡፡
- **የረዥም ጊዜ ብድር**፡- የረዥም ጊዜ ብድር ከ5 ዓመት በላይ የብድር መመለሻ ጊዜ ያለው ሲሆን ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ማሽነሪዎች ለመግዣ ወይም የማምረቻ ቦታ ለመገንባት የሚውል ነው፡፡

2.4.1.2. የኦቨር ድራፍት ብድር

ይህ የብድር ዓይነት ደንበኛ በባንክ ካስቀመጠው (ካለው) ገንዘብ በላይ እስከተወሰነ መጠን ድረስ ለእለት እንቅስቃሴው ብር እንዲያወጣ የሚያስችል ነው፡፡ ይህ የብድር ዓይነት በጊዜ ላይ ተመርኩዞ ከሚሰጥ

ብድር በሁለት ባህሪያት ይለያል፡፡ የመጀመሪያው ብድሩን ለመክፈል ቀድሞ ኘሮግራም የተያዘለት አለመሆኑ እና ሁለተኛው ደግሞ የመክፈያ ጊዜው ክፍት መሆኑ ነው፡፡ ይሁንና ባንኩ በድርጅቱ እንቅስቃሴ ያልረካ ከሆነ በፈለገው ጊዜ ብድሩ እንዲመለስለት ይጠይቃል፡፡ የወለድ መጠኑ የሚሰላውም በወሩ ውስጥ አንድ የኦቨር ድራፍት ደንበኛ ከባንኩ ባወጣው እና ወደ ባንክ ሂሳቡ ባስገባው መጠን ልዩነት ነው፡፡

2.4.1.3. ኦቨር ድሮዋል

ይህ የብድር ዓይነት በኦቨር ድራፍት ላይ ከተመደበለት ብር በላይ ለአስቸኳይ እና ያልተገመተ የገንዘብ እጥረት ማቃለያ የሚፈቀድ የብድር ዓይነት ነው፡፡ ድርጅቱ የኦቨር ድራፍት የብድር ዓይነት ከተመቻቸለት በኂላ ባልተጠበቀ ሁኔታ የገንዘብ እጥረት ቢገጥመው የኦቨር ድሮዋል ብድር እንደገና ሊመቻችለት የሚችልበት አሰራር ነው፡፡ ሆኖም ግን ለዚህ ብድር የሚከፈል የወለድ መጠን ከሌሎቹ ከፍ ያለ ነው፡፡

2.4.1.4. ለማስመጣት የሚሰጥ የመተማመኛ ሰነድ (ሌተር ኦፍ ክሬዲት)

ይህ ዓይነቱ ብድር አንድ አስመጪ ውጭ ሀገር ካለ ላኪ ጋር እቃ ለማስመጣት ይዋዋልና እቃውን ውጭ ያለው ድርጅት መጫኑን የሚያሳይ ሰነድ ለባንኩ ሲያቀርብ ባንኩ አስመጪውን በመወከል የሚከፍልበት የብድር ዓይነት ነው፡፡ ጠቅላላ የግዢና ሽያጭ ውለታዎች የሚፈጸሙት በአስመጭና ላኪዎች መካል ይሆናል፡፡

2.4.1.5. የባንክ የዋስትና ብድር

ይህ የብድር ዓይነት ባንኩ የተወሰነ ገንዘብ ለሚመለከተው ግለሰብ/ድርጅት ለመክፈል ዋስትና የሚገባበት ሲሆን ይህን ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው አመልካች/ ተበዳሪው በውለታው መሰረት ለመፈጸም የገባውን ቃል ሳያከብር ሲቀር ነው፡፡

ከሚሰጡ የዋስትና ሰነዶች መካከል፡-

- የቅድመ-ክፍያ ዋስትና (Advance Payment Guarantee)
- የጨረታ አፈጻጸም ዋስትና (Performance Guarantee)
- የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid/Tender Bond)
- የሪቴንሽን ዋስትና (Retention Guarantee)
- የቀረጥ ክፍያ ዋስትና እና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል፡፡

2.4.2. በወለድ የሚሠጥ የብድር አገልግሎት

የፋይናንስ ተቋማት ብድር ሲሰጡ ገንዘቡ በባንክ ቢቀመጥ ሊያስገኝ የሚችለውን የወለድ ገቢ፣ የተበዳሪው የብድር ታሪክ እና ብድር በተሰጠበት መስክ ላይ ሊመጣ የሚችለውን የአደጋ ስጋት (risks)፣ ሌሎች ባንኮች የሚሠጡበትን የወለድ መጠን (market condition)፣ የብድር መመለሻ ጊዜ፣ የብድር

መጠን፣ ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች፣ ወዘተ ታሳቢ በማድረግ የብድር ወለድ ያስቀምጣሉ። አዲስ ወደ ስራ የሚሰማሩም ይሁን ነባር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለስራቸው ብድር ቢፈልጉ የብድር ጥያቄ የሚያቀርቡበት ባንክ በሚያስቀምጠው የወለድ መጠን መሰረት የብድር ተጠቃሚ ይሆናሉ።

2.4.3. ወለድ አልባ የብድር አገልግሎት

የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ሀይማኖታዊ ዕሴቶችን በጠበቀ ሁኔታ ለተበዳሪዎች ፋይናንስ የሚያቀርቡበት አሰራር በመተግበር ላይ ይገኛሉ። ከእነዚም መካከል **ሙዳራባሃ** (mudarabaha: profit and loss sharing partnership)፣ **ሙሻራካ** (musharaka: profit and loss sharing joint venture)፣ **ኢጃራ** (ijarah: leasing)፣ **ዋዲያ** (wadiah: safe keeping)፣ **ሙራባሃ** (murabaha: cost plust finance)፣ **ታካፉል** (takaful: Islamic insurance) ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ከወለድ ነጻ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በአገራችን ያሉ ባንኮች በሚጠቀሙባቸው የወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

2.4.4. የብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎች

አዲስ ተሻሽሎ በወጣው የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሠረት እንዲሁም የንግድ ህጉ ባስቀመጣቸው የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው የሚገኙ ወይም አዲስ ወደ ስራ ለመግባት የንግድ ፈቃድ የወሠዱ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ተቋማቱን ቅድመ-ሁኔታ እስካሟሉ ድረስ የብድር ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። ከዋና ዋና ንዑሳን የስራ መስኮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-

- የእንጨትና ብረታ ብረት ውጤቶች ማምረት ስራ፣
- የቀርከሃ ውጤቶች ማምረት ስራ፣
- ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ማምረት ስራ፣
- የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረት ስራ፣
- የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ማምረት ስራ፣
- የአግሮፕሮሰሲንግ ውጤቶች ማምረት ስራ፣
- የኮንስትራክሽን ግብዓት ማምረት ስራ፣
- ጌጣ ጌጥ እና የማዕድን ውጤቶች ማምረት ስራ፣
- የእደ-ጥበብ ውጤቶች ማምረት ስራ፣

2.4.5. ብድር ለማግኘት የተቀመጡ ቅድመ-ሁኔታዎች

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በብድር ሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን በፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ በተዘጋጁ መሥፈርቶች መሠረት የሚለዩ ይሆናል:: በአገራችን በሚገኙ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት መካከል የብድር ቅድመ-ሁኔታዎችን አስመልክቶ ልዩነቶች ሊኖሩ ቢችሉም በአብዛኛው ከሚጠየቁት ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

- ህጋዊ የንግድ ፈቃድ፤
- አዋጭነት ያለው የንግድ ስራ ዕቅድ፤
- ብድር በጠየቀበት የስራ መስክ ስራውን እንዴት እንደሚሰራ በቂ ግንዛቤ ያለው፤
- የብድር ዋስትና ማቅረብ፤
- የኢንተርፕራይዙ አባላት የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው፤ መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው፤ እድሜያቸው ከ18 በላይ የሆኑ፤
- መልካም የተበዳሪነት ታሪክ ያላቸው፤
- ቅድመ-ብድር ቁጠባ የቆጠቡ ወይም ከብድር በፊት ለመቆጠብ ፈቃደኛ የሆኑ፤
- ነባር ኢንተርፕራይዞች ከሆኑ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ የሚችሉ፤ የግብር ግዴታቸውን ለመወጣታቸው ማረጋገጫ፤
- የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር፤
- ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች በባለቤትነት የተያዘ ንግድ ከሆነ የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ፅሁፍ፤
- የሚሰማሩበት የስራ መስክ አዋጪ የሆነ፣ በኢኮኖሚም ቢሆን ትርጉም የሚሰጥ፣ በሕግና በአካባቢ ጥበቃ ተቀባይነት ያለው እንዲሁም በማህበረሰቡ የሚፈለግ መሆን አለበት፡፡

2.5. የቅድመ-ብድር ተግባራት

2.5.1. የማስተዋወቅ ሥራ

የብድር አገልግሎቱ የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር በመፍታት ለምርትና ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ማደግ ብሎም ለአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ሊጫወት የሚችለውን ሚና ከፍ ለማድረግ ለአስፈጻሚ አካላት እና ለኢንተርፕራይዞች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በመፍጠር በስፋትና በተደጋጋሚ መስራት ይጠይቃል፡፡ በዚህ የማስተዋወቅ ተግባር ስለቁጠባ ምንነት ዓላማና አስፈላጊነት፣ ስለ ቁጠባ ዓይነቶች እና ስለሚያስገኙት ጠቀሜታ፣ ስለ ሂሳብ መዝገብ፣ ስለ ፋይናንስ አስተዳደር፣ ስለ ንግድ ሥራ ዕቅድ ጠቀሜታ እና አዘገጃጀት፣ ስለ ብድር ዓይነቶች፣ በብድር አሰጣጥ ሂደት ሊሟሉ ስሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ስለ ብድር አሰጣጥና ሂደቱ፣ ስለ ብድር

አጠቃቀምና አመላለስ ወዘተ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በግንዛቤ ፈጠራ እና የማስተዋወቅ ስራችን ወቅት የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡

1) ከአምራች ኢንተርፕራይዞች ጋር የሚደረጉ ውይይቶችና ኮንፈረንሶች በማዘጋጀት፣
2) ኢንተርፕራይዞቹ በሚሳተፉባቸው ኤግዚቢሽና ባዛሮች ላይ በመሳተፍና ተገኝቶ በማወያየት፣
3) በኤሌክትሮኒክስና የህትመት ሚዲያዎች በመጠቀም፣
4) በአበዳሪ ተቋማት ድረ-ገጾች፣ በተቋማት የማህበራዊ ገጾች መረጃዎችን በማሰራጨት ወዘተ፤

2.6. የንግድ ሥራ ዕቅድ ማቅረብ

አነስኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎት ጥያቄያቸውን ለማቅረብ የንግድ ሥራ ዕቅድ አንዱ ቅድመ-ሁኔታ ሲሆን ይህም በዋነኝነት በኢንተርፕራይዙ ባለቤት የሚዘጋጅ ሆኖ አስፈላጊ ሲሆን በአቅራቢያቸው በሚገኙ የዘርፉ ባለሙያዎች በሚደረግላቸው የቴክኒክ ድጋፍ አዘጋጅተው ያቀርባሉ፡፡ የንግድ ስራ ዕቅድ ለማቅረብ የሚጠየቅበት ፎርማት ከአንዱ የፋይናንስ ተቋም ወደ ሌላው የተወሰኑ ልዩነቶች ሊኖሩት የሚችል ሆኖ በአብዛኛው ማጠቃለያ (Executive summary)፣ የፕሮጀክቱ ዳራ (Project background)፣ የገበያ ትንተና (marketing plan)፣ የምርት ዕቅድ ትንተና (production plan)፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል አስተዳደር (Organizational and management plan) እና የፋይናንስ ዕቅድን (Financial plan) በማካተት ይዘጋጃል፡፡

❖ የንግድ ሥራ ዕቅድ መገምገሚያ መስፈርቶች

አበዳሪው የፋይናንስ ተቋም በአካባቢው ያሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ በመዳሰስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመገምገሚያ ነጥቦችን መሠረት በማድረግ የቀረበውን የንግድ ሥራ ዕቅድ የአዋጭነት ትንተና ያካሄዳል፡፡

- ደንበኛው የተሰማራበት የሥራ መስክ ያለው የገበያ አዋጭነት፣ የግብአት አቅርቦት፣ በሥራው ላይ ያለው ልምድ፣ ያደረገው ቅድመ ዝግጅት፣ በአካባቢው ያሉ ተፎካካሪዎችና የገንዘብ እንቅስቃሴውን በመገምገም፣
- ለምርቱ/አገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት መገኘቱንና ዘላቂነት ያለው መሆኑን፣ ለምርቱ/አገልግሎቱ በቂ ገበያ መኖሩን፤ እንዲሁም ከንግዱ የሚገኘው ትርፍ ብድሩን የመመለስ አቅሙን በመገምገም፣
- በተሰማሩበት የምርት ወይም የአገልግሎት ሥራ መስኮች የክህሎት ሥልጠና የወሰዱ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣

- ንግዱ የሚካሄድበት የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ለሥራው ምቹና ተሥማሚ እንዲሁም ህጋዊ መሆኑን በማረጋገጥ፣
- ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የኢንተርፕራይዙን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች እንዲሁም ሥጋቶችና መልካም አጋጣሚዎች በመተንተንና ደንበኛው በተሠማራበት የሥራ መስክ ይኖራል ተብሎ የታሰበውን የሥጋት መጠንና የብድር የመመለስ አቅም ደረጃ በማውጣት፣
- የቀረቡትን አጠቃላይ የብድር ሂደት ሰነዶች ከተቋሙ የብድር አሠራር አንጻር በመተንተን፣
- የንግዱን ህጋዊነትና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ፤
- የንግዱ ባለቤቶች ንግዱን ለማካሄድ ያላቸውን የአመራር ብቃት በመገምገም፣
- ንግዱ ሊፈጥር የሚችለውን የሥራ ዕድልና ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን ማህበራዊ ፋይዳዎች በመገምገም፣
- ህጋዊነትን ከማረጋገጥ አንፃር የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ማድረጋቸውን በማረጋገጥ፣
- ኢንተርፕራይዞች ለሚወስዱት ብድር በቂና አስተማማኝ ዋስትና ያላቸው መሆኑን በማገምገም፣
- ፈቃደኛ፣ ታታሪና መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው አባላት ያሉት ስለመሆኑ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻቸው የታወቀ መሆኑና በማረጋገጥ፣
- ያለፈ ብድር አመላለስ ታሪካቸው ጥሩ የሆነና ቁጠባ ለመቆጠብ ያደረጉትን ጥረት በማረጋገጥና ግብር ስለመክፈላቸው ማስረጃ ያቀረቡ መሆናቸውን በማየት፣
- ነባር ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከሆኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድና ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫና የተመረመረ የሒሳብ ሰነድ ያቀረቡ መሆነቸውን በማረጋገጥ፣

2.7. ከብድር አመልካቾች የሚጠበቁ ማሥረጃዎች

የብድር አመልካቾች ለብድር ጥያቄ ሲያቀርቡ በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት አብረው የተለያዩ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

- የሚሰማራበት የሥራ መስክና የብድር መጠየቂያ ማመልከቻ፣
- በቅድመ-ብድር የቁጠባ ሥርዓት መሠረት ቁጠባ መቆጠቡን የሚያሳይ ማሥረጃ፣
- በዋስትና የሚቀርበው የቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት (የሥራ መሣሪያ፣ ቤት፣ ተሽከርካሪ) የባለቤትነት ማረጋገጫ ሠነድ፣
- በዋስትናነት የሚቀርበው የደመወዝ ዋስትና ከሆነ ዋስትናውን የሚወስደው ሰው ከሚሰራበት መ/ቤት የተጻፈ የዋስትና ማረጋገጫ ደብዳቤ፣
- በዋስትና የሚቀርበው ቋሚ ንብረት ከዕዳና ገዳ ነፃ መሆኑን የሚያስረዳ ማሥረጃ፣
- ዋስትናው በብድር ዋስትና ፈንድ የሚሸፈን ከሆነ ከሚመለከተው አካል ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማሥረጃ፣

- በዋስትና የሚቀርበው ተንቀሳቃሽ ንብረት ከሆነ ተንቀሳቀሽ ንብረቱ በመያዣ ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማሥረጃ፣
- በዘመኑ የታደሠ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ፣ የዋና ምዝገባ፣ የግብር ክፍያ ዕዳ የሌለበት ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤
- የአመልካቹን የብድር ታሪክ የሚገልጽና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚሠጥ ማስረጃ፤
- የጋብቻ የምስክር ወረቀት ወይም ትዳር አለመኖሩን የሚያረጋግጥ ማሥረጃ፣
- የታደሠ የቀበሌ መታወቂያ ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

2.8. የብድር ዋስትና አይነቶች

በተበዳሪ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርቡ የዋስትና አማራጮች የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የሚሰጡትን ብድር በወቅቱ እንዲመልሱ ከፍተኛ አስተዋፆ ከማድረጉ በተጨማሪ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎቶች ቀጣይነት እንዲኖረው፤ ለብድር የሚቀርበው ገንዘብ ከተለያዩ የቁጠባ ምንጮች የተሰባሰቡ በመሆናቸውና የብድር መመለስና አለመመለስ ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ህልውና ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው በመሆኑ፤ ማህበረሰቡ በብድር የመጠቀም፣ ብድር ወስዶ በጊዜው የመመለስ ባህልን ለማዳበር ስለሚያግዝ ኢንተርፕራይዞች ለሚወስዱት ብድር ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በአቅማቸው እና ባላቸው ምቹ ሁኔታ (ዕድል) ላይ በመመስረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አማራጭ የዋስትና አይነቶች በመጠቀም የብድር ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2.8.1. በመንግስት የሚሸፈን የብድር ዋስትና

ይህ የዋስትና ዓይነት መንግስት በልዩ ሁኔታ መደገፍ አለባቸው ብሎ ላመነባቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ለማድረግ በማለም ከአበዳሪ ተቋማት ብድር በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ ዋስትናው በመንግስት የሚሸፈንበት አሰራር ሲሆን ይህም ራሱን የቻለ የብድር ዋስትና ስርዓት በመዘርጋት ወይም ለዋስትና የሚውል ፈንድ መድቦ ጥቅም ላይ በማዋል ወዘተ ሊፈጸም ይችላል፡፡ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችም በዚህ መሰል የዋስትና ዕድል መጠቀም የሚችሉበት አሰራር ካለ ማየት ይገባል፡፡

2.8.2. የሦስትዮሽ ውል ስምምነት

በምርት ገዢ፣ አቅራቢና አበዳሪ ድርጅት መካከል በሚደረግ የሦስትዮሽ ውል በመጠቀም ኢንተርፕራይዞች ከአበዳሪ ተቋም ሊበደሩ ይችላሉ:: በዚህ የዋስትና አማራጭ በኢንተርፕራይዝ የተመረተውን ምርት/አገልግሎት ግዢ የሚፈፅመው ሁለተኛ ወገን ምርቱን/አገልግሎቱን ለመግዛት መሥማማቱን፣ የግዢውን ዋጋ የሚገልፅ እና ለአቅራቢ ኢንተርፕራይዞች ክፍያውን ከመፈፀሙ በፊት ለአበዳሪው ተቋም ብድሩን ቀንሶ ለመክፈል መሥማማቱን የሚያረጋግጥ ማሥረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2.8.3. የቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና

ይህ የዋስትና ዓይነት ተበዳሪዎች በግል በሚያቀርቡት የቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና (ቤት፣ ተሽከርካሪ፣ ማሽነሪ ወዘተ) ብድር የሚሠጥበት ነው፡፡

2.8.4. የደመወዝ ዋስትና

ይህ የዋስትና ዓይነት የፋይናስ አቅራቢ ተቋማት በሚያስቀምጡት አሰራር መሰረት ብድር ጠያቂዎች ለሚፈልጉት ብድር የደመወዝ ዋስትና አቅርበው አነስተኛ ብድር የሚበደሩበት ሲሆን በአገራችን የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማትም የሚጠቀሙበት ነው፡፡

2.8.5. የመጋዘን አገልግሎት ዋስትና

በህጋዊ መንገድ የመጋዘን አገልግሎት እንዲሰጥ ከተቋቋመ ድርጅት የምርት ጥራቱ የተረጋገጠና በመጋዘን የተከማቸ ምርት የአገልግሎት ደረሰኝ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ፣ ተበዳሪው እና ምርቱን አስቀማጩ የሚያደርጉትን ሥምምነት እንደ ዋስትና በመያዝ ብድር ይሰጣል፡፡

2.8.6. የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት (Second level land certificate)

ኢንተርፕራይዙ ለሚፈልገው ብድር የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (second level land certificate) በማስያዣነት በማቅረብ ብድር የሚወስድበት የዋስትና አማራጭ ነው፡፡

2.8.7. የጊዜ ገደብ ቁጠባ ዋስትና (fixed time deposit)

ይህ የዋስትና ዓይነት የፋይናንስ ተቋም ላይ የተቀመጠን የጊዜ ገደብ ቁጠባ ለብድር ዋስትና ለመጠቀም ከተቆጠበበት ባንክ ጋር በመነጋገርና ወደ ማይንቀሳቀስ ሂሳብ በመቀየር እና ዋስትና በማድረግ ብድር የሚወሰድበት አሰራር ነው፡፡

2.8.8. የአክሲዮን ምስክር ወረቀት

የፋይናንስ ተቋማት አዋጭ ናቸው ብለው የለዩአቸውን አክሲዮኖች ዋስትና በማድረግ ብድር ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2.9. የብድር መጠን

ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የብድር መጠን እንደተሰማሩበት የሥራ አይነት፣ ብድር የተጠየቀበት ስራ ብድሩን ለመክፈል ያለውን አቅም እና የወሠዱትን ብድር በአግባቡ ለመጠቀም ያላቸውን የገንዘብ አጠቃቀም ብቃት፣ የሚያቀርቡትን የብድር ዋስትና መጠን ወዘተ ታሳቢ በማድረግ በሚጸድቀው የንግድ ሥራ ዕቅድ መሰረት ይወሰናል፡፡ አንድ ተበዳሪ ለብድር ብቁ ለመሆን የሚያስችሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልቶ እስከተገኘ ድረስ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ የቀረበለትን የብድር ጥያቄ በተገቢው መረጃ ላይ ተመስርቶ ከ5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ያጸድቃል፡፡

2.10. በዋስትና የተያዘ ንብረት የመድን ሽፋን

በንግድ ህጉ መሠረት ህጋዊ ዕውቅና ያላቸው አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በተሰማሩበት የሥራ መሥክ በንብረት ላይ ሊከሰት ለሚችል ሠው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋ በዋስትና ላስያዙት ንብረት የተፈቀደላቸው ብድር ከመለቀቁ በፊት የመድህን ግዴታ ሊወጡ ይገባል፡፡ ብድሩ በአንድ ዓመት ተከፍሎ የማያልቅ ከሆነ የመድን ሽፋኑ በየዓመቱ እንዲታደስ ይደረጋል፡፡ ኢንተርፕራይዙ በግንባር ቀርቦ የማያሳድስ ከሆነ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ከራሱ ወጪ በማድረግ የሚያሳድስ ሲሆን በማሳደስ ሂደቱ ወጪ የተደረጉትን ሂሳቦች በሙሉ በቀሪው ብድር ላይ በመጨመር ያስከፍላል፡፡

2.11. የብድር ውል መፈጸም

የብድር ውል ሥምምነት የመፈጸም ተግባር እንደ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ አደረጃጀትና አሰራር የሚወሰን ሆኖ ውሉም በፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ እና ብድር በጸደቀለት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ መካከል ይሆናል፡፡

2.12. ብድር ማሰራጨት

ኢንተርፕራይዞች በቅድመ-ብድር ጊዜ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ ለብድር የፀደቀው ገንዘብ ወደ ተበዳሪዎች የቁጠባ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል ወይም በጥሬ ገንዘብ ይሰጣቸዋል ወይም ኢንተርፕራይዞች እንደሚሰማሩበት የሥራ ዘርፍ እና የግዢ ዕቅድ ከፋይናንስ አቅራቢው ተቋም ጋር በሚኖራቸው የብድር ሥምምነት በተለያየ ጊዜ ይለቀቅላቸዋል፡፡

2.13. የአገልግሎት ክፍያ

ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለሚሰጡት አጠቃላይ የብድር አገልግሎት እያንዳንዱ ተበዳሪ ኢንተርፕራይዝ በፀደቀለት ብድር መሰረት በፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ የሚወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2.14. የብድር ወለድ ምጣኔ

ኢንተርፕራይዞች ለሚበደሩት ገንዘብ የሚከፍሉትን የወለድ ምጣኔ በተመለከተ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማቱ በውስጥ አሰራራቸው ላይ ተመስርተው እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚወስኑት ይሆናል፡፡ ሆኖም የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማቱ የማህበራዊ ኃላፊነታቸውንና ቀጣይነታቸውን በሚያረጋግጥና ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያበረክቱ ዘርፎችን በልዩ ሁኔታ መደገፍ በሚያስችል መልኩ የወለድ ምጣኔውን እንዲወስኑ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡

2.15. የእፎይታ ጊዜ

ተበዳሪ ኢንተርፕራይዞች ብድር ወስደው ወደ ተግባር ከመግባታቸው በፊት ለሥራው አሥፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን ለማጠናቀቅ በሚወስድባቸው ጊዜ በቀጥታ ወደ ምርት አቅርቦት የማይገቡበት

ሁኔታ ስለሚኖር የዕፎይታ ጊዜ ይሠጣቸዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተበዳሪዎቹ ብድሩን ከተበደሩበት ቀን ጀምሮ አበዳሪው ተቋም ባሰራጨው ብድር ላይ ወለድ ያሰላል። ተበዳሪ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች የሚጠበቅባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ሳያሟሉ የዕፎይታ ጊዜ በመስጠት ብድር እንዲወስዱ ማድረግ አላስፈላጊ የሆነ የወለድ እና ተጨማሪ ወጪዎች እንዳያስከትልባቸው ብድር ከመሰጠቱ በፊት ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

2.16. የብድር መመለሻ ጊዜ

አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚሰማሩበትን የሥራ መስክ ግምት ውስጥ በማስገባት የብድር መመለሻ ቆይታ ጊዜው የአጭር ጊዜ፣ የመካከለኛ ጊዜ ወይም የረዥም ጊዜ ሊሆን ይችላል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተወሰደው ብድር ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ባለው የብድር ቆይታ ጊዜ ውስጥ በየጊዜው ብድሩ የሚከፈልበት የመመለሻ ጊዜ (በየወሩ፣ በየሦስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ፣ በየዓመቱ) ከአበዳሪው ተቋም ጋር በሚያደርጉት የብድር ሥምምነት የሚወሰን ይሆናል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ውስብስብ የስራ ባህሪ ታሳቢ በማድረግ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ብድር በሚመቻችበት ሁኔታ ላይ እንዲሁም በየጊዜው ብድሩ የሚመለስበት ጊዜ ሲወሰን ለኢንተርፕራይዞች በቂ የመመለሻ ጊዜ እንዲኖረው በማድረግ በኩል ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል።

ክፍል ሦስት

3. ድህረ-ብድር ተግባራት

በድህረ-ብድር የሚደረግ ድጋፍና ክትትል አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የብድር ተጠቃሚ ሆነው ዘላቂ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲሁም ተወዳዳሪነታቸውን በማሳደግ፣ ተኪ እና ወጪ ምርቶችን በማምረት ለአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ በማድረግ ረገድ የሚጠበቅባቸውን እየተወጡ መሆኑን ከማየት ባሻገር የተበደሩትን ብድር በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ወቅቱን ጠብቀው ብድር እየመለሱ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል።

3.1. ለኢንተርፕራይዞች የሚደረግ ድጋፍና ክትትል

የፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ እና በየደረጃው የሚገኘው የዘርፉ ልማት መዋቅር መደበኛ የጊዜ ሠሌዳ በማውጣት ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ከዚህ አኳያ፦

- ኢንተርፕራይዞች ያለባቸውን ክፍተት በመለየት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠትና ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል፤
- ተበዳሪዎች የወሰዱትን ብድር ወዲያውኑ ለታለመለት ዓላማ እያዋሉ ስለመሆኑ በአካል ማረጋገጥ፣
- ብድር ሲጠይቁ ባቀረቡት የንግድ ሥራ ዕቅድ መሠረት እየተጓዙ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ለሚያቀርቡት ምርት የገበያ ትስስር በመፍጠር እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ መስጠት፣
- ኢንተርፕራይዞቹ በአግባቡ የሂሳብ መዝገብ እየያዙ መሆኑን በመፈተሽ ድጋፍና ምክር መስጠት፣
- የክህሎትና ስራ አመራር አቅማቸውን በማየት የሚኖሩ ክፍተቶችን በስልጠና እንዲሞሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- ኢንተርፕራይዞች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ያሉ ምቹ ሁኔታዎችን እና ስጋቶችን በመለየት እንደየሁኔታው ችግሮችን መፍታትና ምቹ ሁኔታዎችን በበለጠ በመጠቀም ዕድገታቸው እዲፋጠን መደገፍ፣
- የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሁኔታን በመገምገም ድጋፍና ምክር መስጠት፣
- ኢንተርፕራይዞች መደበኛና የውጼታ ቁጠባቸውን በአግባቡ እየፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥና በውጼታ ቁጠባም የበለጠ እንዲጠናከሩ ማበረታታት፣
- የባለድርሻ አካላትን ድጋፍ የሚሹ ጉዳዮችን መለየትና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣

- ኢንተርፕራይዞች በየጊዜው እንዲመልሱ የተቀመጠላቸውን የብድር መጠን በወቅቱ እየመለሱ መሆኑን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፣

3.2. ብድር ማስመለስ

ተበዳሪዎች ብድሩን ለመመለስ በገቡት የውል ሥምምነት መሠረትና በአበዳሪው ተቋም የብድር አመላለስ ሥርዓት መሠረት ብድር መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር፡-

- ኢንተርፕራይዞች ቀጣይነት ያለው የብድር አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉና ለብድር የሚሆን በቂ የገንዘብ አቅርቦት እንዲኖር አስቀድሞ የተሰጡ ብድሮች በመመለሻ ጊዜያቸው መሠረት ሙሉ በሙሉ /100%/ እንዲመለሱ ማድረግ፤
- በፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ያለውን የገንዘብ አቅርቦት ውስንነት ችግር ለመቅረፍና ተደራሽነትን ይበልጥ ለማሳደግ የዘርፉን ልማት የሚያስተባብሩና የሚደግፉ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ጋር በመቀናጀት ለብድር ማስመለስ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤
- ብድሩ ጤናማ በሆነ መልኩ ተመላሽ ሆነ የሚባለው ተበዳሪው ከሥራ እንቅስቃሴው ካገኘው ሽያጭ/ገቢ ላይ ሲመልስ እንጂ ከዋስትና መያዣ ወይንም ከመንግስት ብድር ዋስትና ተመላሽ የተደረገ ብድር አለመሆኑን ተገንዝቦ ሰርቶ እንዲከፍል መደገፍ፤
- ደንበኞች ውዝፍ ከፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በማወያየት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተወስዶ ሊሰራበት ይገባል፡፡

3.3. ማበረታቻ

የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የደንበኞችን የቁጠባ፣ የብድር አመላለስና አጠቃቀም ወዘተ አፈጻጸም በመገምገም ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲያደርጉ በቅንጅትና በቅርበት መስራትና ይህንኑ ለኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ መፍጠር ይገባል፡፡

3.4. ቅጣት

ኢንተርፕራይዞች አስቀድሞ በተስማሙበት እና በተሰጣቸው የብድር መክፈያ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ብድራቸውን የመክፈል ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ይህ ባልሆነበት ጊዜ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙ ባለው መመሪያ መሠረት የቅጣት ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት ኢንተርፕራይዞች የወሰዱትን ብድር በአግባቡ ተጠቅመው በተቀመጠላቸው የመመለሻ ጊዜ መሰረት እንዲከፍሉ መደገፍና በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ክፍል አራት

4. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

4.1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

- የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በማጥናት አማራጭ የፋይናንስ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች በመንደፍ ለተግባራዊነቱም ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣
- የፋይናንስ ተቋማት የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙና አገልግሎታቸውን እንዲያዘምኑ ድጋፍ ማድረግ፣
- ተበዳሪዎች የወሰዱትን ብድር በአግባቡ ስራ ላይ ማዋላቸውን እንዲሁም ብድሩ በወቅቱ መመለሱን አስመልክቶ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን መከታተል፣ መቆጣጠር፤
- የኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር ለማቃለል የሚያስችሉ አሰራችን መቅረጽና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤
- የፋይናንስ ተቋማት ስራቸውን ጤናማ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲያከናውኑ ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ፤

4.2. ገንዘብ ሚኒስቴር

- ለዘርፉ ልማት የሚውል ፈንድ ከልማት አጋር ድርጅቶች በማፈላለግ እና ስምምነት በመፈጸም ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲውል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የዘርፉ ልማት ለአገራዊ ኢኮኖሚ ልማቱ ሊያበረክት የሚችለውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለብድር ሊውል የሚችል ገንዘብ እንዲመደብ ጥረት ማድረግ፤
- የአነስተኛ እና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት በኢኮኖሚው ውስጥ ያበረከቱትን ፋይዳ ጥናት በማድረግ የፖሊሲ ምክረ ሃሰቦችን ማቅረብ፤
- የዘርፉ ልማት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩን በማፋጠን ረገድ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ የሚያግዙ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በመቅረጽ እንዲተገበሩ ማድረግ፤

4.3. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

- የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዱና የሚሻሻሉ የፋይናንስ ህጎችን ማጥናትና ለመንግሥት ማቅረብ፣ ሲፈቀድም በተግባር ላይ እንዲውል ክትትል ማድረግ፣
- ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች የዘርፉን ልማት በፋይናንስ እንዲደግፉና በባለቤትነት እንዲፈጽሙ ማስተባበር፣

- ለዘርፉ ልማት ምቹ የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- በፋይናስ አሰራር እና አተገባባር ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማስተባበር፣
- በዘርፉ ልማት ሚና ያላቸውን አካላት በማቀናጀት ብድር እንዲመቻች፣ ኢንተርፕራይዞች ክፍተትን መሰረት ያደረጉ ድጋፎች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- የሚመለከታቸው አካላት የሚሳተፉበት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣

4.4. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

- የቁጠባና ብድር አቅርቦት የድጋፍ ማዕቀፎች መቅረጽና በሂደትም እንዲሻሻሉ ማድረግ፤
- የብድር ተጠቃሚ የሚሆኑ/የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚፈልጓቸውን ድጋፎች እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት መስራት፤
- የብድር አቅርቦቱን ሊያግዙ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችን በማስተባበር እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥረት ማድረግ፤
- የብድር ተጠቃሚ የሆኑ ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞች የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፤
- የዘርፉን የፋይናንስ ችግሮች ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር ምክረ-ሐሳብ ማቅረብ፤
- የብድር አቅርቦት አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መከታተል፤ በጋራ በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት፤

4.5. ስራና ክህሎት ሚኒስቴር

- የብድር ተጠቃሚ ለሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ብድር ላገኙ እና ተጠቃሚ መሆን ለሚፈልጉ አነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች (በተለይ በሴቶች ለሚመሩ) የኢንተርፕርነርሺፕ ስልጠና መስጠት፤
- ለዘርፉ ልማት ብድር አቅርቦት የሚውል ገንዘብ ከተለያዩ የልማት አጋር ድርጅቶች በጋራ ማፈላለግ፤
- ለዘርፉ ምቹ የፋይናንስ አቅርቦት ስርዓት እንዲዘረጋ በቅንጅትና በትብብር መስራት፤

4.6. የክልል መንግስት፣ የከተማ እና ወረዳ አስተዳደሮች

- የቁጠባን ባህል የሚያሳድጉ ሥራዎችን ከሌሎች የመንግሥት ልማት ዕቅዶች ጋር በማቀናጀት እንዲከናወኑ በበላይነት በማሥተባበር አፈጻጸሙን መከታተልና መደገፍ፤
- ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር በወቅቱ እንዲመልሱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- የቁጠባ አሰባሰብ፣ የብድር ስርጭት፣ የብድር አመላለስ ስራን በቅርበት በመከታተል መደገፍ፤
- ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ብድር የሚውል ገንዘብ ለፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በመመደብ የብድር አቅርቦቱን ተደራሽነት መደገፍ፤

4.7. የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት

- ለደንበኞች ተደራሽነታቸውን ይበልጥ በማስፋት፤ የደንበኞችን የገንዘብ ደህንነት አስተማማኝ በማድረግ፤ ቀልጣፋና ምቹ አሰራርን በመዘርጋት፣ የተለያዩ ጠቀሜታ ያላቸውን የቁጠባ አይነቶች በመቅረፅና አደረጃጀታቸውን የበለጠ ምቹ በማድረግ በቁጠባ ላይ በስፋት መስራት፤
- የቁጠባ አፈፃፀምን ከሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት ጋር በመሆን በየጊዜው በመገምገም አስፈላጊውን የማስተካከያ ዕርምጃ ማድረግ፤ የገንዘብ አቅርቦትን ከብድር ፍላጎት ጋር በማጣጣም ለኢንተርፕራዞች ተደራሽ ማድረግ፤
- ለተመለመሉ ደንበኞች ስለ ብድርና ቁጠባ ጠቀሜታ፣ ስለ ፋይናንስ አስተዳደር እንዲሁም ስለ ብድር አሰጣጡና ብድር አመላለስ ሂደቱ ማሰልጠን፤
- ደንበኞች ብድር ለማግኘት ማሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታና ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
- በወቅቱ ብድርን ገምግሞ ማጽደቅና ብድር ማቅረብ፤
- ውዝፍ እንዳይከሰት በቅርበት መከታተልና ተበዳሪው ብድሩን በወቅቱ እንዲመልስ ማድረግ፤
- የውዝፍ መንስኤዎችን በመለየትና ተከታታይነት ያለው ትንተና በመስራት ውዝፍ ከመበራከቱ በፊት በየደረጃው ያለው አመራር በቂ መረጃ አግኝቶ የተከሰተውን ውዝፍ ለማስመለስ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ወቅታዊ እርምጃ እንዲወስድ በወቅቱ በማሳወቅ ተቀናጅተው መስራት፤

4.8. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት

- ብድር ያገኙ እና ስራቸውን በአግባቡ እየተወጡ ለሚገኙ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች አሰራሩን ጠብቆ በሊዝ ፋይናንስ አሰራሩ የካፒታል ዕቃ በማቅረብ መደገፍ፤
- በቁጠባ እና ብድር ማስመለስ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- ኢንተርፕራይዞች ውጤታማ እንዲሆኑ በፋይናንስ አጠቃቀም እና አስተዳደር ላይ ስልጠና መስጠት፤

4.9. በክልል፣ በዞን በከተማና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የዘርፉ ልማት አደረጃጀቶች

- የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ቁጠባን ለማሰባሰብ የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍና ማስተባበር፤

- ተበዳሪዎች መሰማራት የሚችሉባቸውን የሥራ መስኮች፣ ሊያሰሯቸው የሚችሉ የአደረጃጀት አማራጮች እና በብድር አሰጣጥ ሂደት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤
- በሚሰማሩባቸው የሥራ መስኮች ላይ የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች በመለየት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት እንዲፈቱ ድጋፍ ማድረግ፤
- ስለ ሂሳብ መዝገብ አያያዝና የንግድ ሥራ ዕቅድ ጠቀሜታ እንዲሁም አዘገጃጀት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ መስራትና ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ፤
- ነባር ኢንተርፕራይዞች ለብድር የሚያቀርቡት የኦዲት ሪፖርት ለግብር ከሚያቀርቡት ጋር ተናባቢ እንዲሆን መደገፍና ተናባቢ ሳይሆን ቢገኝ ቅጣት እንደሚያስከትል ማሳወቅ፤
- የተሰራጨ ብድር በወቅቱ እንዲመለስ ከፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- የተበዳሪ ኢንተርፕራይዞችንና የወሰዱትን የብድር መጠን አስመልክቶ ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ሪፖርት ማድረግ፤

ክፍል አምስት

5. የድጋፍ፣ ክትትል እና የግምገማ ስርዓት

አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን በመደገፍ ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ፤ ገቢ ምርትን እንዲተኩ፣ ወጪ ምርትን እንዲያመርቱ ለማስቻል፤ ለዜጎች ዘላቂ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ በማድረግ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ለማድረግ ዘርፉ ያሉበትን ተግዳሮቶች ከመለየት ጀምሮ መፍትሔ እስከ መስጠት የሚደርስ የባለድርሻ አካላት ትብብርና ቅንጅትን የሚጠይቅ ነው፡፡

5.1. የክትትልና ድጋፍ አደረጃጀት

የክትትልና ድጋፍ ስራውን ውጤታማ ለማድረግ በአፈጻጸሙ ላይ በየደረጃው ወቅታዊ ግምገማ በማካሄድና ለሚያጋጥሙ ችግሮች የጋራ መፍትሔ በመስጠት መምራትን ይጠይቃል፡፡ ለዚህም አመች አደረጃጀት ፈጥሮ መምራት የሚያስፈልግ በመሆኑ በአደረጃጀቱ ውስጥ የሚከተሉት አካላት እንዲካተቱ ቢደረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

❖ **ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**

የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የቁጠባና የብድር አቅርቦት ተደራሽነት አፈጻጸምን ከሚመለከታቸው የፌደራል፣ የክልልና ከተማ አስተዳደሮች፣ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በዝርዝር ይገመግማል፣ ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

❖ **የክልል የዘርፉ ልማት አደረጃጀት**

- የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ልማት አፈጻጸም ከሚመለከታቸው የክልል፣ የዞንና የከተሞች አደረጃጀቶችና ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ በዝርዝር ይገመግማል፣ ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
- የብድር አቅርቦትና አመላለስ ሂደቱን የሚከታተል የኮሚቴ አደረጃጀት በመፍጠር በየሩብ ዓመቱ በመስክ ምልከታ ላይ የተመሰረተ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረግ ይገመግማል፣ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ መክሮ የጋራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

❖ **የዞን የዘርፉ ልማት መዋቅር**

በዞኑ/ክፍለ ከተማው ያለውን የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት የቁጠባና የብድር አቅርቦት አፈጻጸም የዞን/ክፍለ ከተማ፤ የወረዳና ከተሞች እንዲሁም የሚመለከታቸው የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በየሩብ ዓመቱ በዝርዝር ይገመግማል፣ ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

❖ **የከተማ/የወረዳ/ቀበሌ አስፈፃሚ አካል**

የስራ ማስኬጃ ብድር በማቅረብና ቁጠባ በማሰባሰብ ሂደት ድርሻ ያላቸው አካላት ስራውን የሚገመግሙበት ቋሚ መርሐ-ግብር በማውጣት ይወያያሉ፣ የብድርና ቁጠባ አፈጻጸም ሪፖርትን ይገመግማሉ፣ ለተከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡

5.2. የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት እና ልውውጥ

- በየደረጃው የአነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱን የሚያስተባብሩ ጽ/ቤቶች እና የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ከተሰራጨ ብድር እና ከተሰበሰበ ቁጠባ ጋር የተያያዙ ዝርዝር መረጃዎችን በአግባቡ እያደራጁ ይይዛሉ፤
- በሁሉም አካላት የተያዙ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት እና ሪፖርት የሚደረጉበት አሰራር በመዘርጋት ወጥ የሆነ ሪፖርት በየወሩ ከወረዳ እስከ ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት እንዲቀርብ ማድረግ፤
- የመረጃ ልውውጡና አያያዙም በዘመናዊ የቴክኖሎጂ አሰራር ሥርዓት የተደገፈ እንዲሆን መስራት፤

5.3. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የቁጠባ፣ ብድር ስርጭትና ማስመለስ ስራ ላይ የባለድርሻ አካላት የላቀ ትብብርና ቅንጅት የሚፈልግ ቢሆንም በዚህ ረገድ ሰፊ ውስንነት ያለ መሆኑ፤
- ስራው የአመራር ቁርጠኝነትን እና ያላሰለሰ ክትትልና ድጋፍን የሚጠይቅ መሆኑ፤
- በኢንተርፕራይዞች በኩል የመቆጠብ ባህላቸው አነስተኛ መሆኑ፣ ብድር ወስዶ ሰርቶ በወቅቱ መክፈል እንዳለባቸው በአመለካከት ደረጃ ያለመያዝ ክፍተት መኖሩ፤
- በፋይናንስ ተቋማት በኩል የማፋክቸሪንግ ዘርፉ ያለበትን ውስብስብ ችግር፣ ለአገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ዘርፉን በልዩ ሁኔታ ያለመደገፍ፤
- አነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለአገር ኢኮኖሚ ልማት ያላቸውን ሚና አሳንሶ ማየት፤

ማጣቀሻ ሰነዶች፣

1. Planning and Development Commision (2020). *10 Years Development Plan.* Addis Ababa

2. **የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት** (2014 ዓ.ም)፣ ***በኢፌዲሪ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር*** *1263/2014*፣ **አዲስ አበባ**

3. National Bank of Ethiopia (2021). *National Financial Inclusion Strategy II.* Addis Ababa

4. **የሚኒስትሮች ምክር ቤት** (2015 ዓ.ም)፣ ***የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት ተግባርና ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር*** *526/2015*፣ **አዲስ አበባ**

5. National Bank of Ethiopia (2023). *Annual Report.* Addis Ababa

አባሪዎች

<u>የብድር መጠየቂያ ማመልከቻ (በመኖሪያ ቤት ዋስትና ለሚሰጥ ብድር የተዘጋጀ ናሙና)</u>

ቀን-------------------------

ለ-------------------ባንክ/ ማይክሮ ፋይናስ ተቋም

ለ--------------------ቅርንጫፍ

<u>አዲስ አበባ</u>፤

ጉዳዩ፤ <u>የስራ ማስኬጃ ብድር አግልግሎት እዲሰጠኝ ስለመጠየቅ</u>፤

አመልካች እኔ ----------------------- የተባልኩት በ----------------------------------ንግድ ስራ የተሰማራሁ የባንካችሁ (የማይክሮፋይናንስ ተቋማችሁ) ደንበኛ ስሆን ለ------------- ስራ ማስፋፊያ እና ስራ ማስኬጃ የሚውል ብር ----------(------) በየ-----------ወር የሚከፈል ሆኖ በ------------------------ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ ብድር ከባንካችሁ (ከማይክሮፋይናንስ ተቋማችሁ) በብድር ማግኘት እችል ዘንድ በዚህ ማመልከቻ ጥያቄያን አቀርባለሁ፡፡ ለብድር ዋስትና የሚሆን ንብረት በ-------- ከተማ ----------- ክፍለ ከተማ ---------------------- ወረዳ --------- የቤት ቁጥር ------------ የካርታ ቁጥር የሆነ እና በ------------- ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት ያቀርብኩኝ መሆኑን እየገለፅኩ የጠየቅኩት ብድር እዲፈቀድልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

የብድር መጠየቂያ ቅፅ (ለናሙና የተዘጋጀ)

ቀን_____________

ለ…….. ባንክ/ማይክሮፋይናንስ ተቋም_____________________________________ ቅርንጫፍ

እኔ/እኛ የብድር አመልካቾች የብድር ጥያቄዬን/አችንን ሳቀርብ/ስናቀርብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ/ጥን ለጥያቄዬ/አችን በጎ ምላሽ እንደሚሰጥ በመተማመን ነው፡፡

1. የብድር አመልካች ሙሉ ስም____
2. የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ሙሉ ስም____
3. የንግድ ስራው የኢኮኖሚ ዘርፍ____
4. የንግድ ስራው ዓይነት ____
5. ድርጅቱ የንግድ ፈቃድ ያገኘበት ዓ.ም________________________________
6. የድርጅቱ አመሰራረት ዓይነት (በግል ኃላፊነት የሚመራ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፤ አክሲዮን ማህበር፤ የሽርክና ማህበር፤ ሌላ ከሆነ ይጠቀስ) ________________________________
7. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር____
8. አድራሻ

አድራሻ	ከተማ	ወረዳ	ቀበሌ	ቤት ቁጥር	ስልክ ቁጥር	የፖሳታ ሳጥን ቁጥር /ኢሜይል
የስራ						
የመኖሪያ						

9. ድርጅቱ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል /በአክሲዮን ማህበር የተቋቋመ ከሆነ

የአክሲዮን ብዛት	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ	የአክሲዮኑ መዋጮ የተከፈለበት ሁኔታ	
			በጥሬ ገንዘብ	በአይነት

10. ድርጅቱ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል/ በአክሲዮን ማህበር የተቋቋመ ከሆነ

የዋና ዋና ባለአክሲዮኖች ስም	የአክሲዮን ድርሻ	በሌላ ድርጅት ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ (ካለ)	
		የድርጅቱ ስም	የአክሲዮን ድርሻ

11. የተጠየቀው ብድር ሁኔታ

የብድሩ መጠን (በብር)	የብድሩ ዓይነት (በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል፤ ኦቨር ድራፍት፤ ቅድመ-ጭነት፤ የመሳሰሉት)	የሚከፈልበት ጊዜ	የአከፋፈል ሁኔታ (በየወሩ በየሦስት ወሩ የመሳሰሉት)	በየጊዜው የሚከፈል የክፍያ መጠን (በብር)

12. ብድሩ የተፈለገበት ዓላማ/ የተጠየቀበት ምክንያት (ለስራ ማስኬጃ፤ ለአዲስ ፕሮጀክት፤ ለፕሮጀክት ማስፋፊያ፤ ለተሽከርካሪ/ማሽን/ህንፃ መግዣ የመሳሰሉት) ______________________

____

____

____

13. የብድር ክፍያ ምንጭ

____

____

____

14. ለብድሩ የቀረበ ዋስትና

የባለንብረቱ ሙሉ ስም	የዋስትና ዓይነት (መኖሪያ ቤት፤ የንግድ ህንፃ፤ ተሽከርካሪ የመሳሰሉት)	የዋስትናው የገበያ ዋጋ/ግምት/	መረጃ (ሊብሬ፤ የካርታ ቁጥር፤ የመሳሰሉት)	ዋስትናው የሚገኝበት አድራሻ

15. ባንክን የሚመለከት መረጃ

15.1 ብድር ጠያቂው በአሁኑ ጊዜ ከባንኩ ቅርንጫፎች ጋር የብድር ግንኙነት ካለው የሚሞላ (ከሌለው የለውም ተብሎ ይፃፍ) ____

____

____

የቅርንጫፉ ስም	የብድሩ ዓይነት	የብድር መጠን	የብድሩ ዋስትና		ብድሩ አሁን ያለበት ሁኔታ
			ዓይነት	ግምት	

15.2 ብድር ጠያቂው በአሁኑ ጊዜ ከሌሎች ባንኮች ጋር የብድር ግንኙነት ካለው የሚሞላ (ከሌለው የለውም ተብሎ ይፃፍ)

____

____

____

የባንኩ እና ቅርንጫፍ ስም	የብድሩ ዓይነት	የብድር መጠን	የብድሩ ዋስትና		ብድሩ አሁን ያለበት ሁኔታ
			ዓይነት	ግምት	

16. ድርጅቱ በኃላፊነቱ የተወሰነ የግል/በአክሲዮን ማህበር ተቋቋመ ከሆነ/

16.1 የብድር ጠያቂው ዋና ዋና ባለቤቶች ወይም ባለአክሲዮኖች ከባንኩ ቅርንጫፎች ጋር የብድር ግንኙነት ካላቸው የሚሞላ (ከሌላቸው የላቸውም ተብሎ ይፃፍ

____

____

____

የባለቤት/ባለአክዮን ስም	የቅርንጫፍ ስም	የብድሩ ዓይነት	የብድር መጠን	የብድሩ ዋስትና		ብድሩ አሁን ያለበት ሁኔታ
				ዓይነት	ግምት	

16.2 የብድር ጠያቂው ዋና ዋና ባለቤቶች ወይም ባለአክሲኖች ከሌሎች ባንኮች ጋር የብድር ግንኙነት ካላቸው የሚሞላ (ከሌላቸው የላቸውም ተብሎ ይፃፍ)

____

____

____

የባለቤት/ባለአክሲዮን	የባንኩና	የብድሩ	የብድር	የብድሩ ዋስትና	ብድሩ አሁን

ስም	ቅርንጫፍ ስም	ዓይነት	መጠን	ዓይነት	ግምት	ያለበት ሁኔታ

17. በግልና በጋራ ባለቤትነት ለሚመሩ ድርጅቶች ብቻ
    17.1 የቤተሰብ እና የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና

የዘመድ ስም	የዝምድናው ዓይነት	የባንኩ ተበዳሪ ናቸውን? (ናቸው ወይም አይደሉም)	ተበዳሪ ከሆኑ የቅርንጫፍ ስም

18. የንግድ ድርጅቱ ዋና ዋና ደንበኞች እና አቅራቢዎች

ዋና ዋና ድንበኞች ስም	ዋና ዋና አቅራቢዎች ስም

19. በባንኩ ቅርንጫፎች ውስጥ የሚገኝ የአመልካቹ የባንክ ሂሳብ ቁጥር

የባንክ ሂሳብ ቁጥር	ቅርንጫፍ ስም

እኔ/እኛ ስሜ/ስማችን ከዚህ በታች የተገለፀው የብድር ጥያቄ አቅራቢ/ዎች ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች በሙሉ በንፁህ አእምሮ እና እምነት በትክክል የተሞሉ እና እውነት መሆናቸውን አረጋግጣለሁ/እናረጋግጣለን፡፡

ይህ የብድር ጥያቄ የቀረበለት የ…….. ባንክ የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ከሚመለከታቸው አካላት ማረጋገጥ እና ማመሳከር የሚችል መሆኑን በፊርማዬ/በፊርማችን አረጋግጣለሁ/እናረጋግጣለን፡፡

የአመልካች/ቾች ስም	የስራ ድርሻ /ኃላፊነት	ፊርማ	ቀን
________________________	______________________	________________	________________

ክብ ማህተም